www.abyssinialaw.com



7ኛ አመት ቁጥር 17

7th Year 17

ባህር ዳር ሰኔ 7 ቀን 1994 ዓ.ም

Bahir Dar 14 th ,June 2002

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የ ፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |



| ማውጫ<br>ደንብ ቁጥር 2/1994 ዓ.ም | Contents<br>Regulation No.2/2002 |
|---|---|
| የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ደንብ | The Amhara National Regional State prosecutors administrative Regulation Amendment Regulation |

## ደንብ ቁጥር 2/1994 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዐቃቢያነ ሕግን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል የወጣ የክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ

## REGULATION NO.2/2002

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE PROSCUTORS ADMINISTRTIVE REGULATION.

www.abyssinialaw.com



በስራ ላይ ያለውን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዓቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 13/1992 ዓ.ም ከተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግስት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና የብሔራዊ ክልሉን መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም አንቀጽ 26 ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዓቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 2/1994 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

   የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዓቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 13/1992 ዓ.ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   ሀ. የደንቡ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 7 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፡፡

   7. " ረዳት ዓቃብያነ ሕግ" ማለት እንደነገሩ ሁኔታ የወረዳ ወይም የዞን ዓቃቤ ሕግ ሆኖ ለሹመት የሚያበቃ የትምህርት ደረጃ ወይም በቂ የአገልግሎት ጊዜ ሣይኖረው በዞን ወይም በክልል ደረጃ ተመድቦ የሚያገለግል ባለሙያ ነው፡፡

   ለ. ከደንቡ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 7 ቀጥሎ

Whereas, it has been found essential to amend the Amhara National Regional State prosecutors' Administration Executive committee Regulation No13/2000, so as to make it conform with the Revised constitution of the Regional state;

Now , therefore, the Council of the Regional government of the Amhara National Regional State pursuant to the powers vested in it under article 58 Sub article 7 of the 2001 revised National Regional constitution and article 26 of the proclamation No. 60/2001, a proclamation to reorganize determine the powers and duties of executive organs of the Regional state, thereby issues this amendment regulation as follows:

1. **Short Title**

   This Regulation may be cited as" The Amhara National Regulation state prosecutors' Administrative Regulation amendment council of Regional government Regulation No 2/2002"

2. **Amendments**

   The Amhara National Regional state prosecutors administrative Executive committee Regulation No 13/2000 is amended as follows

   A. Sub –article 7 of article 2 of the regulation is hereby deleted and replaced by the following new sub-article.

   7" Assistant prosecutor" shall mean any woreda or Zonal prosecutor serving in a prosecutorial office either on Zonal of Regional levels, as the case may be, without having acquired prior professional training or working experience required for the appointment to those prosecutorial post.

   B. The following new sub Article 8 is added after

www.abyssinialaw.com



የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 8 የገባ ሲሆን በዚሁ ተጨማሪ ድንጋጌ ምክንያት ቀሪዎቹ ድንጋጌዎች ንዑስ አንቀጽ 9፣10፣11ና 12 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

8. " ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ "ማለት ከምክትል ቢሮ ኃለፊ በታችና ከደረጃ 3 የክልል ዓቃቤ ሕግ በላይ ሆኖ በመመሪያ ኃላፊነት የተሾመ ሕግ በላይ ሆኖ በመምሪያ ኃላፊነት የተሾመ ባለሙያ ነው፡፡

ሐ. የደንቡ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ይህ ደንብ በፍትህ ቢሮ ኃላፊው እና በምክትሉ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

መ. የደንቡ አንቀጽ 6 ድንጋጌ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6 ተተክቷል፡፡

## 6. <u>ስለ ዓቃብያነ ሕግ አመራረጥ</u>

በዚህ ደንብ መሠረት በማንኛውም የዓቃቤ ሕግ የሥራ መደብ ላይ የሚመደቡ ዐቃብያነ ሕግን ሹመት በሚመለከት የሚደረገው የማወዳደርና የመምረጥ ተግባር በክልሉ ጉባዔ ይከናወናል፡፡

ሠ. የደንቡ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ተሠርተው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ተተክተዋል፡፡

sub Article 7 of article 2 of the regulation and the remaining provisions are re-arranged two new metrically stand as sub- articles 9,10,11 and 12 because of the entry of this supplementary provision.

8. " Assistant prosecutor General" shall mean a professional appointed as a department head with a status below the rank of the deputy Bureau head and above grade III Regional public prosecutor.

C. Sub – article 2 of Article 3 of this regulation is hereby deleted and replaced by the following new Sub- article2.

2. Notwithstanding the provision of sub article 1 of this article hereof, this regulation may not apply to the head and Deputy Head of Justice Bureau.

D. The Provision of Article 6 of the regulation is hereby deleted and replaced by the following new article 6.

## 6. <u>Selection of prosecutors</u>

All the activities regarding competition for and selection to any prosecutorial employment position to be occupied by prosecutors at all levels either through assignment or appointment; shall be carried out by the Regional commit ion, pursuant to these regulation

E. The provisions of sub-article 1 and 2 of article 7 of the Regulation are hereby deleted and replaced by the following new sub- articles 1and 2.

www.abyssinialaw.com



1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሠረት በክልሉ ጉባዔ የሚመረጡ ዐቃብያነ ሕግ በቢሮ ኃላፊው ይሾማሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በብሔራዊ ዞኖች ውስጥ የሚመደቡ ዐቃብያነ ሕግ ለሹመት ከመቅረባቸው በፊት የብሔረሰብ ዞኑ አስተዳደር ም/ቤት ስለ ዐቃብያነ ሕጉ ሹመት አስተያየት እንዲሰጥ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

ረ. በደንቡ አንቀጽ 28 ከፊደል ተራ ቁጥር ሐ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ ቁጥር መ ተጨምሯል፡፡

መ. በዚህ አንቀጽ ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ-ሐ የተዘረዘሩት መደቦች ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚደረግ ሽግሽግ ተፈጻሚ የሚሆንበት መመሪያ በክልሉ ጉባዔ ተጠንቶ ወደ ፊት ይወሰናል፡፡

ሰ. የደንቡ አንቀጽ 29 ፊደል ተራ ሐ በሚከተለው አኳኋን ተሻሽሏል፡፡

ሐ. ዘመጀመሪያው ምደባ በኋላ በመስሪየ ቤቱ የአቋም መሻሻል በመደረጉ ምክንያት ምደባውን ለመለወጥ በቂ በሆነ መጠን የሥራ መደቡ ተግባርና ኃላፊነት ሲለወጥ ከብሔራዊ ክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ጋር በመመካከር ከዚህ ቀደም የተመደቡለትን የሥራ መደቦች በማናቸውም ጊዜ እንደገና ሊመደብ ይችላል፡፡ ሆኖም የምደባው ለውጥ የሚያስከትለውን የማስተካከያ ገንዘብ እንደገና በተመደበው የሥራ መደብ መስሪያ ቤቱ ከተፈቀደለት በጀት ላይ ለመክፈል ሲችል ብቻ ነው፡፡

1. Prosecutors selected by the Regional Commission pursuant to article 6 of this regulation shall be appointed by the Head of the Bureau.
2. Without prejudice to the provisions of sub article 1 of this article here of, the opinion of the Nationality Zonal Administrative Councils shall be required prior to the appointment or assignment of prosecutors in such Zones.

F. Anew Sub- article D is added following sub-article C of Article 28 of the regulation.

d. The Guideline as regard's the implementation of shifts and transfers from one category of employment to anther as described from A-C under this article hereof shall afterwards be studied and thereby issued by the Regional commission.

G. The provision of sub- article C of Article 29 of the regulation is hereby amended as follows:

c. whenever, after the initial arrangement, the duty and responsibility of a certain post of employment is substantially altered in consequence of a possible change of structure in the Bureau warranting the re-arrangement of posts, the Bureau may re-arrange such acknowledged posts in consultation with the council of the National Regional Government Nevertheless, such a re-arrangement is materialized only when it is possible to cover the difference of financial expense incurred as a result of the change from the allotted budget.

www.abyssinialaw.com



ሸ. የደንቡ አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ተሰርተው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተተክተዋል፡፡

1. የክልል ጉባዔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የቢሮ ኃላፊ ……………….. ሠብሳቢ

ለ. ምክትል ቢሮ ኃላፊ ……… ም/ሰብሳቢ

ሐ. ከረዳት ጠቅላይ አቃብያነ ሕግ አንዱ … አባልና ፀሐፊ

መ. ደረጃ 3 የክልል ዐቃቤ ሕግ አንድ …. አባል

ሠ. ደረጃ 2 የክልል ዐቃቤ ሕግ አንድ ……አባል

ረ. ከዞን ፍትህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃለፊዎች አንድ ተወካይ ……. አባል

ሰ. ደረጃ 2 የዞን ዐቃቤ ሕግ አንድ ….. አባል

ሸ. ከወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊዎች አንድ …ተወካይ"

ቀ. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር …….ተወካይ

በ. ከክልሉ የሕግ ጠበቆች ማህበር አንድ … ተወካይ"

ተ. ከብዙሃን ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ሁለት ተወካዮች …. አባላት

በዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ቁጥር ሐ እስከ ፊደል ተራ ቁጥር ሸ የተመለከቱት የክልል ጉባዐ አባላት የሚሰየሙት የየደረጃው አቃብያነ ሕግ በሚያካሂዱት ምርጫ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የቢሮ ኃለፊው በጉባዔው የሚሣተፉ 2 ተጨማሪ ዐቃብያነ ሕግን ሊሰይም ይችላል፡፡

H. The provisions of cub-articles 1 and 2 of Article 100 of the regulation are hereby deleted and --- by the following new sub-articles 1and 2.

1. The Regional Commission shall have the following members:

   a. The Bureau Head ……... Chair person
   b. The Deputy Bureau Head …. V chair person;
   c. One of the Assistant prosecutors general member and secretary ;
   d. Grade three Regional prosecutor one.... member;
   e. Grade two Regional prosecutor one ….. member;
   f. A representative from among zonal justice branch offices ……. Members;
   g. Grade two Zonal prosecutor one –member:
   h. A representative from among woreda Justice offices….. member:
   i. The regional police commissioner:
   j. A representative of the Regional Bar Association …. Member:
   k. Two representative from mass organizations and civic societies …. Members.

Members of the Regional commission indicated from letter C-H of this sub- article hereof shall be designated as such an election to be carried out by prosecutors of all level.

2. Notwithstanding the provisions of sub- article 1 of this Article hereof, the Bureau head may designate two additional prosecutors to participate as members of the Regional commission.

www.abyssinialaw.com



ቀ. የደንቡ አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 ድንጋጌዎች ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑሣን አንቀጾጽ 1፣2 እና 3 ተተክተዋል፡፡

1. ደረጃቸው ከምክትል ቢሮ ያለፈ በታች የሆኑትን አቃቢያነ ሕግ ቅጥር ፣ ሹመት ፣ የደረጃ እድገት ስንብትና የመሳሰሉትን በሚመለከት አጥንቶ በቢሮው ኃላፊው አማካኝነት ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. የዐቃቢያነ -ሕግን የሥራ ኃላፊነት ደረጃቸውን እንደገና የመመደብን፣ ድርጅታዊ መዋቅርን፣ የደመወዝ ስኬልንና የእርከን ጭማሪን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማድረግ ወይም በማስጠናት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣
3. ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ ልዩ ልዩ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችንና የአሠራር ሥነ- ሥርዓቶችን እያዘጋጀ በቢሮው በኩል ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

በ. የደንቡ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፡፡

1. የዞን ንዑስ ጉባዔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የዞን ፍትህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ .... ሰብሳቢ
   ለ. ከደረጃ 3 የዞን ዐቃብያነ ሕግ አንዱ አባልና ፀሐፊ፣
   ሐ. ደረጃ 2 የዞን ዐቃቤ ሕግ አንድ ..... አባል፣
   መ. ደረጃ 3 የወረዳ ዐቃቤ ሕግ አንድ ..... አባል፣
   ሠ. ደረጃ 2 የወረዳ ዐቃቤ ሕግ አንድ .....

I. The provisions of sub articles 1,2 and 3 of Article 101 of the regulation are hereby deleted and replaced by the following new sub-articles 1,2and 3.

1. Studies the employment, appointment, promotion, dismissal and the like affairs with regard to prosecutors below the rank of the Deputy Bureau Head and have same enforced by the Bureau Head.
2. Studies and causes to be studied, matters concerning the re-arrangement of prosecutorial posts of employment grade, organizational structure, salary scale and annual salary increments and submit same to the council of the regional Government;
3. Prepares and issues various guidelines and working procedures for the implementation of this Regulation by the Bureau.

J. Sub article 1 of Article 102 of the regulation is hereby deleted and replaced by the following new sub-article 1.

1. The Zonal Sub- commission shall have the following members:
   a. Head of zonal Justice branch office… chair person:
   b. One of the Grade three zonal prosecutors … member and secretary:
   c. Grade two zonal prosecutor one …..member;
   d. Grade three woreda prosecutor one.. member;
   e. Grade two woreda prosecutor one …

www.abyssinialaw.com



አባል፣

ረ. የዞን ፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ ………… አባል፣

ሰ. ከዞን አስተዳደር ጽ/ቤት አንድ ተወካይ …አባል፣

ሸ. የዞን ጠበቆች ቅርንጫፍ ማህበር አንድ ተወካይ .. አባል

ቀ. የብዙሃን ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ሁለት ተወካዮች … አባላት፣

በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ ቁጥር ለ እስከ ፊደል ተራ ቁጥር ሠ ድረስ የተመለከቱት የዞን ጉባዔ አባላት የሚሰየሙት በዞኑ ውስጥ የሚገኙት አቃቢያነ -ሕግ በሚያካሂዱት ምርጫ ይሆናል፡፡

## 4. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትመ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባሕር ዳር**

**ሰኔ 7 ቀን 1994 ዓ.ም**

**ዮሴፍ ረታ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**

member;

f. Zonal police office head …… member;

g. A representative from the office of zonal administration …. member;

h. A representative from the zonal branch Bar Association ….. member;

i. Two representatives from mass organizations and civic societies …. Members.

Members of zonal sub-commission indicated from b-e of this sub- article hereof shall be designated as such in an election to be carried out by all the prosecutors residing within the zone concerned.

## 3. Effective Date

This Regulation shall come in to force as of the day of its publication in the Ziker Hig gazette of the regional state.

**Bahir dar**

**This 14 th day of June 2002**

**Yosef Retta**

**Head of Government**

**Of the Amhara National Regional state**